# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** جبهة تحرير اورومو

Gaafa: 05/08/2017
Date: تاريخ

Lakk.:11/stm/abo/2017
No.: رقم

**ህዝቦችን እየዋሹ መኖር ሊገታ ይገባል!**

***የኦነግ መግለጫ***

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የኦሮሞ ህዝብ ለመሰረታዊ ጥያቄው ምላሽ እስካላገኘ ድረስ ከሙብት ጥያቄ ባነሱ ችግሮች ላይ ማተኮር ኣስፈላጊ ኣለመሆኑን ያስገነዝባል። የወያኔ/ኢህኣዴግ መንግስት የሙስናን ኣጀንዳ ያነሳው እውነት መፍትሄ ሊያበጅለት ሳይሆን የህዝቦች ሃሳብ በዚህ ጉዳይ እንዲያዝ ለማድረግ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለይ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ይህንን ሴራ በመገንዘብ ትግሉን በማፋፋሙ ላይ እንዲያተኩር ኦነግ ያሳስባል። ኣሮጌውን ዘራፊና ሌባ በኣዲስ መተካት መፍትሄ ኣይሆንም። ዘላቂው መፍትሄ ችግሩን ከመሰረቱ ማስወገድ ነው።

ዘራፊውና ጨቋኙ የወያኔ ስርዓት ህዝባዊ ኣመጽ ሲበረታበት የህዝቦችን ኣመጽ ለማብረድ ሲል በህዝቦች የተነሱት ችግሮች መኖራቸውንና መንግስትም ችግር እንዳለው ኣምኖ በመቀበል "እራሴን ኣርማለሁ፡ ያሉት ችግሮችንም እፈታለሁ" በሚል ቅጥፈት ለማታለል በመሞከር ይታወቃል። በዚህም ጊዜ ሽምቶ ያለውን ተቃውሞ ለማብረድ ብቻም ሳይሆን ህዝቦችን በሃሳብ ለመከፋፈል ይገለገልበታል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከተካሄዱት ተቃውሞዎች ውስጥ በኦሮሞ ህዝብ እንደተካሄደው ተቃውሞ የተቀናጀና የወያኔን መንግስት ውጥረት ውስጥ የከተተ የለም። ከዚህም የወያኔ መንግስት እንደኣማራጭ የወሰደው በማባበል ያለውን ተቃውሞ ማብረድ ሳይሆን ወታደራዊ እርምጃ በመውሰድ ማፈን መሆኑ በተደጋጋሚ ታይቷል። በዚህም በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ዜጎች ተገድለዋል፥ በኣስር ሺዎች እስር ቤት ታጉረዋል። በተለያዩ እስር ቤቶች በተለይም በ"ማዕከላዊ" እስር ቤት ለኣሰቃቂ ምርመራና ቶርቸር የተዳረጉት ዜጎች በሺዎች ይቆጠራሉ።
ለህዝባቸው መብት በመቆማቸውና ለፍትህና ለዲሞክራሲ በመፋለማቸው ለሰቆቃ የተዳረጉ፡ የተገደሉና በተፈጸመባቸው ቶርቸር ለከፋ ኣካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት የተዳረጉት ዜጎች ቁጥር የትየለሌ ነው።

ሁሉም የማዕከላዊ እስር ቤት ግድግዳዎች በኦሮሞ ልጆች ደም ተቀብተዋል። የመጸዳጃ ቤቶች በሙሉ ላለፉት 26 ዓመታት የኦሮሞ ልጆች ደም ሰፈስስባቸው ዛሬን ደርሰዋል። የወያኔን የደህንነት ቢሮ የሚመሩ እንደነክንፈ ገብረመድሕንና ጌታቸው ኣሰፋ ላለፉት 26 ዓመታት ኦሮሚያን በበላይነት በኣገዛዛቸው ስር በማዋል የሚታወቁትና ኦፒዲኦን በመምራት እኩይ ዓላማቸውን በማሳካት ላይ የተሰማሩ፡ ከደሕንነት ኣባሎቻቸው ጋር ለ26 ዓመታት ለፈሰሰው ደም በቀደሚነት ተጠያቂዎች ናቸው። እንደኩማ ደመቅሳ፡ ኣባዱላ ገመዳ፡ ሙክታር ከድር፡ ኣስቴር ማሞና ሌሎችም በርካቶች በዚህ እኩይ ተግባር ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የኦፒዲኦ ኣመራር ኣባላትም ተጠያቂዎች ናቸው።

P.O. Box 6973 Asmara, Eritrea Tel 2911 110236 Email: Caalchis@gmail.com, *www.oromoliberationfront.org*

ሁሉም የኢትዮጵያ በመንግስታት በዚህ “ማዕከላዊ” በሚባለው የምርመራ ቢሮ መጠቀማቸው ኣንድ ቢያደርጋቸውም እንደወያኔ የተገለገለበት ግን የለም። ይህን ምድራዊ ሲዖል የኢምፓዬሪቷ ምክር ቤትና ፍርድ ቤትም መቆጣጠርና ማዘዝ ኣለመቻሉ ደግሞ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚደርሰው ጉዳት እጅጉን የከፋና የሰፋ እንዲሆን ኣስችሎታል።
ይህ ኣሰቃቂ ምርመራ የሚፈጸምበት ቦታ(ማዕከላዊ) ለፍትህ የቆሙትን ዜጎች ሞራል ለመስበር የሚገለገሉበት፡ ከእስርቤቱ በህይወት የወጡትም ለኣካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ተዳርገው በቤተሰብና በሃገር ላይ ሸክም እንዲሆኑ የሚደረግበት የሰቆቃ ማዕከል ነው። በዚህ ፋሽስታዊ ድርጊት በሚፈጸምበት የምርመራ ቢሮ ውስጥ የሚተገበረው ሰቆቃ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ በእስረኞች ደም በየግድግዳዎቹ ከተጻፉት ጽሁፎች መረዳት ይቻላል።

ከ2002 እስከ 2017ዓም ለመብታቸው በሚታገሉ ዜጎች ላይ የተፈጸመው ግድያ ምን ያህል ኣሰቃቂ እንደሆነና የተገደሉት ዜጎች ቁጥር በርካታ መሆኑን ማስታወስ በቂ ነው። በተለይም በጥቅምት ወር 2016ዓም ቢሾፍቱ ላይ በተከበረው የኢሬቻ በዓል ላይ ሆን ተብሎ በተፈጸመ ኣረመኒያዊ ተግባር በዜጎች ላይ የደረሰውን ኣሰቃቂ እልቂት ያላወገዘ ኣልነበረም። ከማውገዝም ባሻገር እንደተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፡ የኣውሮፓ ህብረት፡ ሂውማን ራይትስ ዎች፡ ኣምነስቲ ኢንተርናሽናል፡ የኣሜሪካ የምክር ቤት ኣባላት ያሉና የመሳሰሉት የደረሰው እልቂት ዘግናኝ በመሆኑ በነጻና ገለልተኛ ኣካል እንዲጣራ እስከፊንፊኔ ድረስ በመሄድ የወያኔን መንግስት ቢጠይቁም ምላሽ ኣላገኙም። ይህ ጥያቄ እንዳይነሳም ወያኔ ኣድሎኣዊ የሆነ ቡድን በመሰየም ህዝቡን ተጠያቂ የሚያደርግ የሃሰት ሪፖርት እንዲቀርብ በማድረግ ይህንን ወንጀል የፈጸሙት እንዳይጠየቁና ወንጀሉ ተሸፋፍኖ እንዲቀር ኣድርጓል።

በዚህም ለፈሰሰው የኦሮሞ ዜጎች ደም በመፈጸሙና በማስፈጸሙ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው እንደጌታቸው ካሳ፡ ደብረጽዮን ገብረሚካኤል፡ ኣባይ ጸሃዬ ያሉና የስርዓት የጦር ኣዛዦች ለህግ ተጠያቂነት ሳይቀርቡ መቅረታቸው ብቻ ሳይሆን፡ መግደልና ማሰቃየቱን እንዲቀጥሉበት ተበረታትተዋል።

ከኦሮሚያም ውጪ በተለያዩ ክልል መስተዳድሮች ውስጥ የሚፈጸመው ግድያ የወያኔን ማንነት ይበልጥ ያስረዳል። በኣማራ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ ከማንነት ጋር ተያይዞ በተነሳው ጥያቄ የጠፋው የሰው ህይወትና የወደመው ንብረት ከፍተኛ ነው። እንደዚሁ በደቡብ ህዝቦች ክልል፡ በጋምቤላ፡ በሲዳማ፡ በኮንሶና በሌሎችም በርካታ ቦታዎች የተፈጸመው ግድያና እስራት በኢትዮጵያ ህዝቦች ብቻም ሳይሆን በመላው ዓለም ተኮንኗል። በተጨማሪም ከህዝብና ከዓለም እይታ በተሰወረ መልኩ በተለያዩ የኦሮሚያ ወረዳዎችና በሌሎችም የሃገሪቷ ክልል መስተዳድሮች ውስጥ በህዝቦች ላይ የተፈጸሙትን ግድያዎች ብዛት የሚያውቅ የለም።

ፍትሃዊ ትግልን በሃይልና በኣረመኔያዊ እርምጃ የሚያዳክሙ መስሎኣቸው የወሰዷቸው እርምጃዎች ሁሉ ግን በሺዎች የሚቆጠሩ ታጋዮች ወደ ፍልሚያው እንዲቀላቀሉ ኣደረገ እንጂ የትግሉን ጎራ ኣላመነመነውም።

ህዝቦች በያዟቸው ፍትሃዊ ጥያቄዎች ላይ በቁርጠኝነት ጸንተው ኣመጻቸውንና ኣንገዛም-ባይነታቸውን እንዲቀጥሉ ኣደረጋቸው እንጂ ገዢዎች እንዳለሙት ለስርዓቱ እንዲንበረከኩ ኣላደረጋቸውም። ስለሆነም በኣሁኑ ጊዜ ይህን የበሰበሰ ስርዓት ለማቆየት እንደልማዳቸው የህዝቦችን ትኩረት ኣቅጣጫ ለማስቀየር ያረጀ-ያፈጀ ስልታቸውን ይዘው ተነስተዋል።

ህዝቡን በህልም እንጀራ ለማጥገብ ሃገር እናለማለን በማለት ላይ ይገኛሉ። የእድገት ጸር በሆነው ሙስና ላይ ዘመቻ ስለጀመርን ከኛ ጋር ተሰለፉ በማለት ላይ ናቸው። ይህ ሁሉ ቅጥፈት ግን ከህዝቦች የተሰወረ ኣይደለም፥ የሙስና ጉዳይ ሁል ጊዜ ውጥረት ውስጥ ሲገቡ የሚነሳ በመሆኑ። እውን በሙስና ላይ የሚዘምቱ ከሆነ እንደነስብሃት ነጋ፡ ኣዜብ መስፍን፡ ኣባይ ጽሃዬ፡ በረከት ስምዖን፡ ኣርከበ ዑቅባይና ወዘተ ያሉትን በቁጥጥር ስር በማዋል ማሳየት ኣለባቸው።

ባዶ እጃቸውን መጥተው የቪላዎችና ፎቆች ባለቤት የሆኑትን የወያኔ ጄኔራሎችና የበታች መኮንኖችን ለፍርድ በማቅረብ ዘመቻ መጀመራቸውን ማሳየት ነበረባቸው። ኣባቶቻቸውን ከለላ በማድረግ የህዝብና የሃገር ሃብት ዘርፈው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ያጠራቀሙትን የወያኔ ሹማምንት ልጆች በቁጥጥር ስር በማዋል በሙስና ላይ መዝመታቸውን ማሳያት ነበረባቸው። ከዚህም በተጨማሪ በቱባ-ቱባ የወያኔ ባለስልጣናት ወደ ውጩ የተጋዘው በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ እንዲመለስ ቢደረግ ምናልባት ዘመቻው በሙስና ላይ የሚካሄድ ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ከዚህ ውጪ ኣሁን እየተፈጸመ ያለው ካሁን ቀደም የህዝቦችን የትኩረት ኣቅጣጫ ለማስቀየር ሲሰራ የነበረው ድራማ ቀጣይ ኣካል ሆኖ ይቀራል። ከዚህም በተጨማሪ ቀንደኛ ዘራፊዎችንና ሌቦችን ለማዳን ሲባል ትናንሾቹን ለመሰዋት የቀረበ ከንቱ ቀልድ ከመሆን ሊያልፍ ኣይችልም።
የህዝቦች መብት ባልተከበረበት፡ የወያኔ ቡድን መሰረታዊ ዓላማ ዝርፊያ በሆነበት፡ ሙስናን እናጠፋለን ማለት በራስ መቀለድ ነው።
በኣሁኑ ወቅት ኣንገብጋቢውና ዋነኛው ለህዝቦች የመብት ጥያቄ ምላሽ መስጠት እንጂ በሌለ ዘመቻ ህዝቦችን ለማወናበድ ኣልያም የትኩረት ኣቅጣጫውን ለማስቀየር መሞከር ኣይደለም።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የኦሮሞ ህዝብ ለመሰረታዊ ጥያቄው ምላሽ እስካላገኘ ድረስ ከመብት ጥያቄ ባነሱ ችግሮች ላይ ማተኮር ኣስፈላጊ ኣለመሆኑን ያስገነዝባል። የወያኔ/ኢህኣዴግ መንግስት የሙስናን ኣጀንዳ ያነሳው እውነት መፍትሄ ሊያበጅለት ሳይሆን የህዝቦች ሃሳብ በዚህ ጉዳይ እንዲያዝ ለማድረግ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለይ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ይህንን ሴራ በመገንዘብ ትግሉን በማፋፋሙ ላይ እንዲያተኩር ኦነግ ያሳስባል። ኣሮጌውን ዘራፊና ሌባ በኣዲስ መተካት መፍትሄ ኣይሆንም። ዘላቂው መፍትሄ ችግሩን ከመሰረቱ ማስወገድ ነው።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**
**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**
**ነሃሴ 5, 2017ዓም**